# የማንማርበት

ያገርና የህዝብ ፣ እውነተኛ ፍቅሩ
እንቅልፍ የነሳቸው ፣ ሞተው ያስተማሩ
በደም ባጥንታቸው ፣ አገር ያስከበሩ
እንደሻማ ቀልጠው ፣ ብርሃን ያበሩ
በተግባር በስራ ፣ እያስመሰከሩ
አንቱ የተባሉ ፣ አገርን ያኮሩ
ዛሬ እንዳሉ ሁሉ ፣ ትላንትም ነበሩ ።

በከተማም ይሁን ፣ በጫካው በዱሩ
ፍፃሜውን ሳናይ ፣ ገና በጅምሩ
ልብን የሚያማልል ፣ ወሬ ስላወሩ
የተናገሩትን ፣ ሳናየው በግብሩ
ሰማይ እየሰቀልን ፣ ስለደሰኮሩ
እንደነ ልደቱ ፣ ኋላ የሚያሳፍሩ
ተንሸራታች ዜጋ ፣ ሆነው እንዳይቀሩ
መጠንቀቅ አይከፋም ፣ ካለፈው መማሩ ።

ያልሆነ እንደሆነ ፣ አድርጎ መሳሉ
ስሙ ገነን ሲል ፣ ሰማይ ላይ መስቀሉ
ቅርፊቱን እያዩ ፣ ሳይታይ አስኳሉ
ያንንም ይሄንን ፣ ማለት ተቀበሉ
ያገረሸ እንደሆን ፣ የትላንት አመሉ
ካልተወራረሱ ፣ ተግባርና ቃሉ
ምንም ፋይዳ የለው ፣ መወነጃጀሉ
የከፋ ይሆናል ፣ ለዚ አከፋፈሉ ።

ጠንቅቆ መራመድ ፣ አስተውሎ መቅረብ
አይመጣምን ትቶ ፣ ይመጣልን ማሰብ
ሁሉን በተገቢው ፣ እንዳይሰፋ እንዳይጠብ
አስፈላጊም ሲሆን ፣ መቆጠብ መሰብሰብ
ገደብ ይኑርለት ፣ ለፍቅር ሆነ ለጸብ ።

የማንማርበት ፣ የያዘን አባዜ
ጩኸት ሲበረታ ፣ ስናይ ባለጊዜ
ለመጣው አጃቢ ፣ እየሆንን ሚዜ
ያላሰብነው ሲሆን ፣ ማፈር ሁልጊዜ ።

ታዛቢው

February 8, 2018